27 “ኃጢአት የሠራውና ባለማወቅም ተሳስቶ
ከእግዚአብሔር ትእዛዛት አንዱን የተላለፈው
ሰው ከተራው ሕዝብ ወገን ከሆነም ፤ 28 ኃጢ
አት መሥራቱን እንዳወቀ ወዲያውኑ ምንም
ነውር የሌለባት እንስት ፍየል ለኃጢአት መሥ
ዋዕት ያቅርብ ። 29 እጁንም በእንስሳይቱ ራስ
ላይ ይጫን ፤ ከመሠዊያው በስተ ሰሜን ለሚቃ
ጠል መሥዋዕት የሚቀርቡ እንስሳት በሚታረዱ
በት ስፍራ ይረዳት ። 30 ካህኑም የእንስሳይቱን
ደም በጣቱ እያጠቀሰ በመሠዊያው አራት ማእ
ዘን ጕጦች ላይ ያኑር ፤ ከዚህም የተረፈውን
ደም በመሠዊያው ሥር ያፍስሰው ። 31 ለደኅን
ነት የሚሆን የኅብረት መሥዋዕት የሚቀርቡ
እንስሳትን ስብ በመግፈፍ በሚፈጽመው ዐይነት
የዚህችንም እንስሳ ስብ ሁሉ ገፍፎ ያስወግድ ፤
መዓዛው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መሥዋ
ዕት አድርጎም በመሠዊያው ላይ ያቃጥለው ፤
በዚህ ዐይነት ካህኑ ስለዚያ ሰው የኃጢአት ስር
የት መሥዋዕት ያቀርባል ፤ ያም ሰው ኃጢአቱ
ይቅር ይባልለታል ።
32 “አንድ ሰው ስለ ኃጢአቱ ስርየት የበግ
መሥዋዕት ማቅረብ ቢፈልግ ፥ ምንም ነውር
የሌለባት እንስት ትሁን ። 33 እርሱም በእንስሳ
ይቱ ራስ ላይ እጁን ይጫን ፤ ከመሠዊያው በስ
ተሰሜን በኩል ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚቀ
ርቡ እንስሳት በሚታረዱበት ስፍራ ይረዳት ፤
34 ካህኑም የእንስሳይቱን ደም በጣቱ እያጠቀሰ
በመሠዊያው አራት ማእዘን ጕጦች ላይ ያኑር ፤
ከዚህም የተረፈውን ደም በመሠዊያው ሥር
ያፍስሰው ፤ 35 ከዚህም በኋላ ለደኅንነት የሚ
ሆን የኅብረት መሥዋዕት የሚቀርቡ እንስሳትን
ስብ በመግፈፍ በሚፈጽመው ዐይነት የዚህች
ንም እንስሳ ስብ ሁሉ ገፍፎ ያስወግድ ፤ እርሱ
ንም ለእግዚአብሔር ከሚቀርበው የምግብ መባ
ጋር በመሠዊያው ላይ ያቃጥለው ፤ በዚህም ዐይ
ነት ካህኑ ስለዚያ ሰው የኃጢአት መሥዋዕትን
ያቀርባል ፤ ያም ሰው ኃጢአቱ ይቅር ይባልለ
ታል ።

## ምዕራፍ 5

### የበደል መሥዋዕት የሚቀርብበት ምክንያት

1 “አንድ ሰው በፍርድ አደባባይ በይፋ ምስ
ክርነት እንዲሰጥ መጥሪያ ደርሶት ስላየው
ወይም ስለሚያውቀው ነገር ተገቢውን ማስረጃ
ሳይሰጥ ቢቀር በደል ስለሚሆንበት የኃጢአት
ማስተስረያ መሥዋዕት ማቅረብ ይገባዋል ።
2 “አንድ ሰው ባለማወቅ ማናቸውንም በሥ
ርዓት የተከለከለ ርኩስ ነገር ለምሳሌ የአውሬ ፥
የቤት እንስሳ ወይም በደረቱ እየተሳበ የሚንቀሳ
ቀስ ፍጥረት በድን ቢነካ ፥ ያደረገውን ስሕተት
ካወቀበት ጊዜ አንሥቶ በደል ስለሚሆንበት የኃ
ጢአት ማስተስረያ መሥዋዕት ማቅረብ ይገባ
ዋል ።
3 “አንድ ሰው ባለማወቅ ምንም ዐይነት
ይሁን ከሰውነት የሚፈስ አንዳች ርኩስ ነገር
ቢነካ ፥ ያደረገውን ስሕተት ካወቀበት ጊዜ አን
ሥቶ በደል ስለሚሆንበት የኃጢአት ማስተስረያ
መሥዋዕት ማቅረብ ይገባዋል ።
4 “አንድ ሰው ለክፉም ሆነ ለደግ ስለ
ምንም ነገር ያለጥንቃቄ በግዴለሽነት ስእለት
ቢሳል ፥ ያደረገውን ስሕተት ካወቀበት ጊዜ አን
ሥቶ በደል ስለሚሆንበት የኃጢአት ማስተስረያ
ማቅረብ ይገባዋል ።
5 “አንድ ሰው በደል በፈጸመ ጊዜ ኃጢአ
ቱን መናዘዝ አለበት ፤ 6 ስለ በደሉም እንስት
በግ ወይም ፍየል ለእግዚአብሔር መሥዋዕት
አድርጎ ያምጣ ፥ ካህኑም ተቀብሎ ለዚያ ሰው
ኃጢአት ማስተስረያ ይሰዋለት ።
7 “አንድ ሰው በግ ወይም ፍየል ማቅረብ
ካልቻለ ግን ሁለት ርግቦች ወይም ሁለት ዋኖ
ሶች ፥ አንደኛይቱን ስለ ኃጢአት ለሚቀርብ
መሥዋዕት ፥ ሁለተኛይቱንም የሚቃጠል መሥ
ዋዕት አድርጎ የበደሉን ዕዳ ይክፈል ዘንድ ለእግ
ዚአብሔር ያምጣ ። 8 እርሱም እነዚያን አም
ጥቶ ለካህኑ ይስጥ ፤ ካህኑም ከሁለቱ ወፎች አን
ዷቱን ራስዋን ሳይቈርጥ አንገትዋን ቆልምሞ
ለበደል መሥዋዕት ያቅርብ ፤ 9 ከደሙም ጥቂት
ወስዶ በመሠዊያው ጐን ይርጨው ፤ የተረፈው
ንም ደም በመሠዊያው ሥር ያፍስሰው ፤ ይህም
ኃጢአትን የሚያስወግድ መሥዋዕት ይሆናል ።
10 ሌላይቱንም ወፍ በሥርዓቱ ሕግ መሠረት
የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ ያቅርብ ፤ በዚ
ህም ዐይነት ካህኑ ስለ ኃጢአት የሚሠዋውን
መሥዋዕት ያቀርባል ፤ በደል የሠራውም ሰው
ኃጢአቱ ይቅር ይባልለታል ።
11 “አንድ ሰው ሁለት ርግቦች ወይም ሁለት
ዋኖሶች ማቅረብ ባይችል ፥ አንድ ኪሎ የላመ
ዱቄት ስለ ኃጢአቱ ስርየት የሚቀርብ መሥዋ
ዕት አድርጎ ያምጣ ፤ እርሱም ስለ ኃጢአት ስር
የት የሚቀርብ መሥዋዕት እንጂ የእህል መባ
ስላልሆነ የወይራ ዘይት ወይም ዕጣን አይጨም
ርበት ። 12 እርሱንም አምጥቶ ለካህኑ ይስጠው ፤
ካህኑም ከዚያ ዱቄት በእፍኙ ወስዶ ሁሉም
ለእግዚአብሔር የቀረበ መሆኑን በማመልከት
ለእግዚአብሔር ከሚቀርበው የምግብ መባ ጋር
በመሠዊያው ላይ በሚገኘው እሳት ያቃጥለው ፤
እርሱም ኃጢአትን የሚያስወግድ መሥዋዕት
ይሆናል ። 13 ካህኑም በዚህ ዐይነት ስለዚያ ሰው
ኃጢአት ማስተስረያ መሥዋዕትን ያቀርባል ፤
ያም ሰው ኃጢአቱ ይቅር ይባልለታል ፤ የቀረው
ዱቄት የእህል መባ በሚቀርብበት ዐይነት ለካ
ህኑ ይሁን ።”

4፥27-31 ፡- ዘኍ. 15፥27-28 ።

በመሠዊያው ላይ ሰባት ጊዜ ረጨ፤ በዚሁ ዐይ
ነት ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተለዩ ይሆኑ
ዘንድ በመሠዊያውና ለእርሱ መገልገያ በተሠ
ሩት ዕቃዎች ሁሉ ላይ እንዲሁም በመታጠቢ
ያው ሳሕንና በሳሕኑ ማስቀመጫ ላይ ረጨ።
12 የቅባቱንም ዘይት በአሮን ራስ ላይ በማፍሰስ
ቀብቶ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተለየ በማ
ድረግ የክህነት ሹመት ሰጠው፤ 13 ቀጥሎም
ሙሴ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት የአሮንን
ወንዶች ልጆች ወደፊት አቅርቦ ሸሚዝ አለበሳ
ቸው፤ በወገባቸውም ዙሪያ መታጠቂያ አድርጎ
በራሳቸውም ላይ ቆብ ደፋላቸው።

14 ከዚህም በኋላ ሙሴ ስለ ኃጢአት ስርየት
መሥዋዕት የሚቀርበውን ኮርማ አመጣ፤ አሮ
ንና ልጆቹ በኮርማው ራስ ላይ እጃቸውን
ጫኑ፤ 15 ሙሴም ሀረደው፤ ከደሙም ጥቂት
በጣቱ ነክሮ የመሠዊያውን አራት ማእዘን
ጕጦች በመቀባት አንጽቶ ቀደሰው፤ ከዚያም
የተረፈውን ደም በመሠዊያው ሥር አፈሰሰው፤
በዚህም ዐይነት መሠዊያውን ለእግዚአብሔር
በመለየት አነጻው፤ 16 ሙሴ በእንስሳው ሆድ
ዕቃ ላይ ያለውን ስብ ሁሉ፥ ጉበቱን እንደ
መረብ ሆኖ የሚሸፍነው ስብ፥ ኵላሊቶቹንና
በእነርሱ ላይ ያለውን ስብ ወስዶ ሁሉንም በመ
ሠዊያው ላይ አቃጠለው። 17 ከኮርማው የቀረው
ንም ቆዳውን፥ ሥጋውንና አንጀቱን ወስዶ እግ
ዚአብሔር ባዘዘውም መሠረት ከሰፈር ውጭ
አውጥቶ አቃጠለው።

18 ከዚያም በኋላ ሙሴ ለሚቃጠል መሥዋ
ዕት የሚቀርበውን የበግ አውራ አመጣ፤ አሮ
ንና ልጆቹ በአውራው በግ ራስ ላይ እጃቸውን
ጫኑ፤ 19 ሙሴም ሀረደው፤ ደሙንም በመሠዊ
ያው አራት ማእዘን ረጨ፤ 20-21 የበግ አውራው
ንም ሥጋ በየብልቱ ቈራረጠ፤ የውስጥ ዕቃው
ንና የኋላ እግሮቹን በውሃ አጠበ፤ እግዚአብ
ሔር ባዘዘውም መሠረት ጭንቅላቱን፥ ስቡንና
የቀረውንም የአውራውን በግ ሥጋ ሁሉ በመሠ
ዊያው ላይ አቃጠለ፤ ይህም የሚቃጠል መሥ
ዋዕት ሽታው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ
የምግብ መባ ነበር።

22 ሙሴም እንደገና ስለ ክህነት ሹመት የሚ
ቀርበውን ሁለተኛውን አውራ በግ አመጣ፤
አሮንና ልጆቹ እጆቻቸውን በራሱ ላይ ጫኑ፤
23 ሙሴ ዐረደው፤ ከደሙም ጥቂት ወስዶ የአሮ
ንን የቀኝ ጆሮውን ጫፍ፥ የቀኝ እጁን አውራ
ጣት፥ የቀኝ እግሩንም አውራ ጣት ቀባ፤
24 ቀጥሎም የአሮንን ልጆች ወደ ፊት አቅርቦ
የቀኝ ጆሮዎቻቸውን ጫፎች፥ የቀኝ እጆቻቸ
ውን አውራ ጣቶችና የቀኝ እግሮቻቸውን
አውራ ጣቶች ቀባ፤ ከዚህ የተረፈውንም ደም
ሙሴ በመሠዊያው ጐን በአራቱም ማእዘን
ረጨው። 25 ስቡን፥ ላቱን፥ ሆድ ዕቃውን የሚ
ሸፍነውን ስብ ሁሉ፥ እንደ መረብ ሆኖ ጉበ
ቱን ከሚሸፍነው ስብ ምርጥ የሆነውን ክፍል፥
ኵላሊቶቹን፥ በእነርሱ ላይ ያለውን ስብና
በቀኝ በኩል ያለውን ወርች ወሰደ፤ 26 ለእግዚ
አብሔር የተለየ ሆኖ እርሾ ያልነካው ቂጣ ከሚ
ቀመጥበትም መሶብ አንድ ኅብስት ወሰደ፤ እን
ዲሁም በዘይት የታሸ አንድ ኅብስትና አንድ
ስስ ቂጣ ወስዶ በስቡና በወርቹ ጫፍ ላይ አኖ
ረው፤ 27 ይህንን ሁሉ ምግብ ወስዶ ለአሮንና
ለልጆቹ በእጃቸው አስያዛቸው፤ እነርሱም ወደ
ላይና ወደ ታች በመወዝወዝ ለእግዚአብሔር
ልዩ መባ አድርገው አቀረቡት። 28 ከዚህ በኋላ
ሙሴ ምግቡን ከእነርሱ ወሰደ፤ ስለ ክህነት
ሹመት መባ እንዲሆን ከሚቀርበው የሚቃጠል
መሥዋዕት በላይ አድርጎ በመሠዊያው ላይ አቃ
ጠለው፤ ይህም መዓዛው እግዚአብሔርን ደስ
የሚያሰኝ የምግብ ቊርባን ነበር። 29 ቀጥሎም
ሙሴ ፍርምባውን ወስዶ ወደ ላይና ወደ ታች
በመወዝወዝ ለእግዚአብሔር ልዩ መባ አድርጎ
አቀረበ፤ ስለ ክህነት ሹመት ከሚቀርበው የበግ
አውራ የሙሴ ድርሻ ይህ ነበር፤ ሙሴ ሁሉን
ነገር እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት አደረገ።

30 ሙሴ ከቅባት ዘይት ጥቂት በመሠዊያው
ላይ ከነበረውም ጥቂት ወስዶ በአሮንና በልጆቹ
እንዲሁም በልብሳቸው ሁሉ ላይ ረጨው፤ በዚ
ህም ሁኔታ ሙሴ እነርሱንና ልብሶቻቸውን ለእ
ግዚአብሔር የተለዩ አደረገ።

31 ሙሴ አሮንንና ልጆቹን እንዲህ አላቸው፥
"ሥጋውን እግዚአብሔር በሚመለክበት በተቀ
ደሰው ድንኳን ደጃፍ ቀቅሉት፤ በዚያም እግዚ
አብሔር ባዘዘው መሠረት ስለ ክህነት ሹመት
መባ ሆኖ ከሚቀርበው በመሶቡ ውስጥ ካለው
ኅብስት ጋር ብሉት። 32 የተረፈ ሥጋም ሆነ
ዳቦ ቢኖር በእሳት አቃጥሉት፤ 33 የክህነት
ሹመታችሁን ሥርዓት ለመፈጸም ሰባት ቀን ስለ
ሚወስድ ይኸው ሥርዓት እስከሚፈጸምበት
እስከ ሰባት ቀን ድረስ እግዚአብሔር ከሚመለክ
በት ድንኳን ደጃፍ አትወጡም። 34 ኃጢአታች
ሁን ለማስወገድ ይህን ዛሬ ያደረግነውን ሥር
ዓት እንድንፈጽም እግዚአብሔር አዝዞናል፤
35 ስለዚህም እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ በመ
ፈጸም ሰባት ቀን ሙሉ ሌሊትና ቀን እግዚአብ
ሔር በሚመለክበት ድንኳን ደጃፍ ትቈያላ
ችሁ፤ ይህን ባታደርጉ ግን ትሞታላችሁ፤ ይህ
ሁሉ እግዚአብሔር ያዘዘኝ ሕግ ነው።" 36 አሮ
ንና ልጆቹም በሙሴ አማካይነት እግዚአብሔር
ያዘዘውን ሁሉ ፈጸሙ።

## ምዕራፍ 9

### አሮን ለእግዚአብሔር ያቀረበው መሥዋዕት

1 ሰባት ቀን የቆየው የክህነት አሰጣጥ
ሹመት በተፈጸመ ማግሥት ሙሴ አሮንንና
ልጆቹን፥ እንዲሁም የእስራኤልን አለቆች

መባ ሆኖ ይቅረብ። 18 ከኅብስቱም ጋር ማኅበሩ
ምንም ነውር የሌለባቸውን የአንድ ዓመት
ዕድሜ ያላቸው ሰባት የበግ ጥቦቶች፥ አንድ
ኮርማና ሁለት ፍየሎች ያምጡ፤ እነርሱም ከእ
ህሉ ቍርባንና ከወይን ጠጁ መባ ጋር የሚቃ
ጠል መሥዋዕት ሆነው ይቀርባሉ፤ ይህም
መሥዋዕት ሽታው እግዚአብሔርን ደስ የሚያ
ሰኝ ይሆናል። 19 ከዚያም ቀጥሎ ስለ ኃጢአት
ስርየት መሥዋዕት አንድ ተባዕት ፍየል፤ ለደኅ
ንነት የሚሆን የኅብረት መሥዋዕት የአንድ
ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሁለት የበግ ጥቦቶች
አቅርቡ፤ 20 ካህኑም ኅብስቱን ከሁለቱ ጥቦቶች
ጋር ወደላይና ወደታች በመወዝወዝ ለእግዚአብ
ሔር ልዩ መባ አድርጎ ያቀርባል፤ እርሱም የካ
ህናቱ ድርሻ ሆኖ ይኖማል፤ እነዚህም ስጦታ
ዎች የተቀደሱ ናቸው። 21 በዚያን ቀን ለአም
ልኮ ተሰብሰቡ እንጂ ምንም ሥራ አትሥሩ፤
በሚመጡት ዘመናት ዘሮቻችሁ በሚኖሩበት
ስፍራ ሁሉ ይህን የሥርዓት መመሪያ ይጠብ
ቃሉ።
22 "የምድራችሁን መከር በምትሰበስቡበት
ጊዜ የእርሻችሁን ድንበር እትጨዱ፤ የመከሩ
ንም ቃርሚያ ለመሰብሰብ ወደ ኋላ አትመ
ለሱ፤ እርሱን ለድኾችና ለመጻተኞች ተዉላ
ቸው፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ።

### የዓመት መባቻ ቀን በዓል
(ዘኍ. 29፥1-6)

23-24 "በሰባተኛው ወር መጀመሪያ ዕለት
ልዩ የዕረፍት ቀን ታከብራላችሁ፤ የመለከት
ድምፅ በምትሰሙበት ጊዜ እግዚአብሔርን ለማ
ምለክ ተሰብሰቡ። 25 ለእግዚአብሔር የምግብ
መባ አቅርቡበት እንጂ በዚያን ቀን ምንም
ሥራ አትሥሩበት።

### የኃጢአት ስርየት ቀን
(ዘኍ. 29፥7-11)

26-27 "ሰባተኛው ወር ከገባ በኋላ ያለው
ዐሥረኛው ቀን የሕዝቡን ኃጢአት ለማስወገድ
ዓመታዊ ሥርዓት የሚፈጸምበት ዕለት ነው፤
በዚያን ዕለት ምንም ነገር አትብሉ፤ ለአምልኮ
ተሰብሰቡ፤ ለእግዚአብሔርም የምግብ መባ
አቅርቡ፤ 28 በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት
የሕዝቡን ኃጢአት የማስወገድ ሥርዓት የሚፈ
ጸምበት ዕለት ስለሆነ በዚያን ቀን ምንም ሥራ
አትሥሩበት። 29 በዚያን ዕለት ምንም ነገር
የሚመገብ ከእግዚአብሔር ወገን እንደ አንዱ
ሆኖ አይቈጠርም፤ 30 በዚያን ዕለት ሥራ የሚ
ሠራ ማንም ሰው ቢኖር እግዚአብሔር ራሱ
በሞት ይቀጣዋል፤ 31 ስለዚህ በዚያን ዕለት
ምንም ሥራ እንዳትሠሩ፤ ይህም የሥርዓት
መመሪያ ዘሮቻችሁ በሚኖሩበት ዘመናት ሁሉ
ተጠብቆ ይኖራል። 32 ወሩ ከገባ ከዘጠነኛው
ቀን የፀሐይ መጥለቂያ ሰዓት ጀምሮ እስከ ዐሥ
ረኛው ቀን የፀሐይ መጥለቂያ ጊዜ ድረስ ምንም
ነገር ሳትበሉ ይህን ዕለት ልዩ የዕረፍት ቀን
አድርጋችሁ ጠብቁት።

### የዳስ በዓል
(ዘኍ. 29፥12-40)

33-34 "የዳስ በዓል ሰባተኛው ወር ከገባ ከዐ
ሥራ አምስተኛው ቀን ጀምሮ እስከ ሰባት ቀን
ድረስ ይከበራል። 35 ከእነዚህም ቀኖች በመጀ
መሪያው ዕለት ለአምልኮ ተሰብሰቡ እንጂ
ምንም ሥራ አትሥሩበት፤ 36 ከሰባቱም ቀናት
በእያንዳንዱ ለእግዚአብሔር የሚቃጠል የም
ግብ መሥዋዕት ታቀርባላችሁ፤ በስምንተኛው
ቀን እንደገና ለአምልኮ ተሰብሰቡ፤ ለእግዚአብ
ሔርም የሚቃጠል የምግብ መሥዋዕት አቅ
ርቡ፤ ይህም ዕለት አምልኮታችሁን የምትፈጽ
ሙበት ቀን ስለሆነ ምንም ሥራ አትሥሩበት።
37 "አምልኮታችሁን ለመፈጸም በአንድነት
ተሰብስባችሁ እግዚአብሔርን የምታከብሩባ
ቸው፥ የምግብ መሥዋዕት፥ የሚቃጠል መሥ
ዋዕት፥ የእህል ቍርባን ሌላም መሥዋዕትና የወ
ይን ጠጅ መባ በሚፈለገው መጠን በየዕለቱ
የምታቀርቡባቸው የሃይማኖት በዓላት እነዚህ
ናቸው፤ 38 እነዚህም በዓላት በሥርዓት ከሚከበ
ሩት ሰንበታት ጋር ተጨማሪ ሆነው የሚከበሩ
ናቸው፤ በእነዚህም በዓላት የሚቀርቡት ስጦታ
ዎች በሥርዓት ከምታቀርቡአቸው ሌሎች ስጦ
ታዎች ጋር ተጨማሪዎች ሆነው የሚቀርቡ
ናቸው፤ ይኸውም ስእለት ሲፈጸምላችሁ፥
ወይም በበጎ ፈቃዳችሁ ለእግዚአብሔር ከምታ
ቀርቡት መባ ጋር ተደምሮ የሚታሰብ ነው።
39 "የምድራችሁን መከር በምትሰበስቡበት
ጊዜ ሰባተኛው ወር ከገባ ከዐሥራ አምስተኛው
ቀን በመጀመር ይህን የደስታ በዓል ለእግዚአብ
ሔር ፊት እስከ ሰባት ቀን ድረስ ታከብራላ
ችሁ፤ መጀመሪያውና ስምንተኛው ቀን ልዩ
የዕረፍት ቀን ይሆናል። 40 በዚያም በመጀመሪ
ያው ቀን ከምድራችሁ ዛፎች ጥቂት ፍሬ፥ የዘ
ንባባ ዝንጣፊና የለምለም ዛፍ ቅርንጫፍ ይዛ
ችሁ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት እየተደ
ሰታችሁ እስከ ሰባት ቀን ድረስ በዓል አድርጉ።
41 እርሱንም እስከ ሰባት ቀን በእግዚአብሔር
ፊት በደስታ አክብሩት፤ ይህም የሥርዓት መመ
ሪያ በዘሮቻችሁ በሚመጡት ዘመናት ሁሉ
ተጠብቆ ይኖራል። 42 መላው የእስራኤል
ሕዝብ እስከ ሰባት ቀን ድረስ በዳስ ይቀመ
ጣሉ፤ 43 ስለዚህም እግዚአብሔር የእስራኤልን
ሕዝብ ከግብጽ ምድር ባወጣበት ጊዜ በዚሁ

23፥22 ፡- ዘሌ. 19፥9-10፤ ዘዳ. 24፥19-22። 23፥26-32 ፡- ዘሌ. 16፥29-34። 23፥33-36 ፡- ዘዳ. 16፥13-15።

ጠላት በአጠገባችሁ ሳይኖር ተደናቅፋችሁ ትወ
ድቃላችሁ፤ 37 ማንም ሳያሳድዳችሁ እንዳችሁ
በአንዳችሁ ላይ ተሰናክላችሁ ትወድቃላችሁ፤
ማንኛውንም ጠላት ተቋቁማችሁ ለመዋጋት
አትችሉም። 38 በስደት ትሞታላችሁ፤ በጠላቶ
ቻችሁም ምድር ተውጣችሁ ትቀራላችሁ።
39 በጠላቶቻችሁ ምድር ከሞት ተርፋችሁ የም
ትቀሩት ጥቂቶቻችሁ በራሳችሁና በቀድሞ አባ
ቶቻችሁ ኃጢአት ምክንያት መንምናችሁ ትቀ
ራላችሁ።

40 "ነገር ግን የእናንተ ዘሮች የራሳቸውን
ኃጢአት፥ እንዲሁም በእኔ ላይ ያመፁትንና
የተቃወሙኝ የቀድሞ አባቶቻቸውን ኃጢአት
ይናዘዛሉ። 41 ምክንያቱም እኔ በእነርሱ ላይ
በቊጣ ተነሥቼ ወደጠላቶቻቸው ምድር እንዲ
ሰደዱ አደርጋቸው ዘንድ ያነሣሡኝ የቀድሞ
አባቶቻቸው ናቸው፤ በመጨረሻም የእናንተ
ዘሮች በትሕትና ራሳቸውን አዋርደው ስለ ዐመ
ፃቸውና ስለ ኃጢአታቸው ፍዳቸውን ቢቀ
በሉ፥ 42 ከያዕቆብ፥ ከይስሐቅና ከአብርሃም
ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳን አስባለሁ፤ ምድሪ
ቱንም ለሕዝቤ ለመስጠት የሰጠሁትን የተስፋ
ቃል አድሳለሁ። 43 ነገር ግን በመጀመሪያ
ምድሪቱ የሚኖርባት ሕዝብ ታጥቶ ፍጹም ዕረ
ፍት ማድረግ ይኖርባታል፤ ሕዝቡም ሕጌን
በማቃለላቸው፥ ትእዛዛቴንም በመናቃቸው
ተገቢ ቅጣታቸውን መቀበል አለባቸው።
44 ይሁን እንጂ በጠላቶቻቸው አገር ሳሉ እንኳ
አስከ መጨረሻ አልተዋቸውም ወይም አልደ
መሰሳቸውም፤ ይህማ ቢሆን ኖሮ ከእነርሱ ጋር
የገባሁትን ቃል ኪዳን አስከ መጨረሻ ባልጠበ
ቅሁም ነበር፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካቸው
ነኝ። 45 እኔ እግዚአብሔር አምላካቸው እሆን
ዘንድ ሕዝቤን ከግብጽ ምድር በማምጣት ኀይ
ሌን ለአሕዛብ ሁሉ በገለጥሁ ጊዜ ከቀድሞ
አባቶቻቸው ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳን እንደ
ገና አድሳለሁ።"

46 ለእስራኤል ሕዝብ ይነግር ዘንድ ሙሴ
በሲና ተራራ ላይ ሳለ እግዚአብሔር የሰጠው
ሕግጋትና ትእዛዛት እነዚህ ናቸው።

## ምዕራፍ 27

### ለእግዚአብሔር ስለሚቀርቡ ስጦታዎች የሚያስረዳ ሕግ

1 ለእስራኤል ሕዝብ ይነግር ዘንድ እግዚአብ
ሔር ለሙሴ የሚከተሉትን የሥርዓት መመሪያ
ዎች ሰጠው፤ 2 አንድ ዐይነት ልዩ ስእለት ቢፈ
ጸምና አንድ ሰው ለእግዚአብሔር ስጦታ ሆኖ
ቢቀርብ ያንን ሰው መልሶ ለመዋጀት ከዚህ
የሚከተለውን ገንዘብ መክፈል ይቻላል፥
3-7 በይፋ በታወቀው ሚዛን ልክ ዕድሜው ከሃያ
አስከ ስልሳ ለሆነ ጐልማሳ 600 ግራም የሚመ
ዝን ጥሬ ብር፤ በዚሁ ዕድሜ ክልል ለምትገኝ
ሴት ሠላሳ ጥሬ ብር፤ ከአምስት እስከ ሃያ
ዓመት ለሆነው ወጣት ሃያ ጥሬ ብር፤ በዚሁ
ዕድሜ ክልል ላሉች ሴት ዐሥር ጥሬ ብር፤ ዕድ
ሜው ከአንድ ወር እስከ አምስት ዓመት ለሆነ
ሕፃን አምስት ጥሬ ብር፤ በዚሁ ዕድሜ ክልል
ውስጥ ለምትገኝ ሴት ሕፃን ሦስት ጥሬ ብር፤
ዕድሜው ከስልሳ ዓመት በላይ ለሆነው ሰው
ዐሥራ አምስት ጥሬ ብር፤ ዕድሜዋ ከስልሳ
ዓመት በላይ ለሆናት ሴት ዐሥር ጥሬ ብር።

8 ስእለት ያደረገው ሰው ይህን ተመን ለመክ
ፈል የማይችል ሆኖ ከተገኘ ያ ለስጦታ የቀረበ
ውን ሰው ወደ ካህኑ ያምጣው፤ ካህኑም ያ
ሰው የሚችለውን ያህል ገምቶ ዝቅተኛ ዋጋ
ያስከፍለው።

9 ስእለቱ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ሆኖ
ለመቅረብ ተቀባይነት ያለው እንስሳ ከሆነ ለእግ
ዚአብሔር የቀረበው መባ ሁሉ የተቀደሰ ይሆ
ናል። 10 ሰውየውም ለዚያ እንስሳ ሌላ ምትክ
ማቅረብ አይገባውም፤ ምትክ አቅርቦ በተገኘ
ጊዜ ግን ሁለቱም እንስሳት ለእግዚአብሔር የተ
ለዩ ይሁኑ። 11 ስጦታው ለእግዚአብሔር መሥ
ዋዕት ሆኖ ለመቅረብ ተቀባይነት የሌለው
በሕጉ መሠረት በሥርዓት ያልነፃ እንስሳ ከሆነ
ግን ሰውየው እንስሳውን ወደ ካህኑ ያምጣ፤
12 ካህኑም የእንስሳውን መልካምነት ወይም
መጥፎነት ገምቶ ዋጋውን ይወስን፤ ያም ዋጋ
የመጨረሻ ይሆናል፤ 13 ባለቤቱም እንስሳውን
መልሶ ለመግዛት ቢፈልግ በዋጋው ላይ በመቶ
ሃያ እጅ ይጨምር።

14 አንድ ሰው ቤቱን ለእግዚአብሔር የተለየ
ስጦታ አድርጎ ሲያቀርብ ካህኑ የቤቱን መልካ
ምነትና መጥፎነት ገምቶ ዋጋውን ይወስን፤
ያም ዋጋ የመጨረሻ ይሆናል። 15 ባለንብረቱ
ያንን ቤት መልሶ ለመግዛት ቢፈልግ ግን በዋ
ጋው ላይ በመቶ ሃያ እጅ ይጨምር።

16 አንድ ሰው ከመሬቱ ከፍሎ ለእግዚአብ
ሔር የተለየ ስጦታ አድርጎ ቢያቀርብ፥ ዋጋው
መሬቱ በሚቀበለው ዘር መጠን ይወሰን፤ ይኸ
ውም ለእያንዳንዱ ሃያ ኪሎ ግራም ገብስ
ዐሥር ጥሬ ብር ይከፈል። 17 መሬቱን የንብረት
መመለሻ ዓመት እንዳለፈ ወዲያውኑ ለይቶ
የሰጠ ከሆነ ሙሉውን ዋጋ መክፈል ይኖርበ
ታል። 18 መሬቱን የሰጠው የንብረት መመለ
ሻው ዓመት ካለፈ ዘግይቶ ከሆነ ግን ካህኑ እስከ
ተከታዩ የንብረት መመለሻ ዓመት ያለውን ቀሪ
ጊዜ በመገመት ዋጋው እንዲቀነስ ያድርግ።
19 መሬቱን የሰጠው ሰው እንደገና መልሶ ለመ
ግዛት ቢፈልግ በዋጋው ላይ በመቶ ሃያ እጅ

26፥42 ፦ ዘፍ. 17፥7-8፤ 26፥3-4፤ 28፥13-14።

